| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | *"ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ 2 ኛ ፦<br>ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ እንሥራ !"* |
| ደራሲ ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ታኅሣሥ ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንው ፡ ቀ፦.2017-002 |
| ማስታወሻ ፤ | *"ክዋኔ"* ፡ ዐምድ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ክዋኔ

CONSTITUTION | دستور

*[በዚህ ፡ ዐምድ ፥ ስለ ፡ ክዋኔ ፡ (ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት) ፡ ጕዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ይቀርቡበታል ። ]*

## ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ 2 ኛ ፦

# ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ እንሥራ !

---

ታኅሣሥ ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድያ ፡ ዐላማ ፥ ኹለተኛው ፡ ረድፍ ፦

*ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ መሥራት !*

ይላል ።

## 3.1 ፤ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ክዋኔ ።

**"ሕገ ፡ መንግሥት"** ፡ ማለት ፡ ያንድ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ የጋራ ፡ ፈቃድ ፡ የኾነ ፡ የሀገር ፡ ክዋኔ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**"ክዋኔ"** ፤ **"ከዊን"** ፡ (በዐማርኛ ፡ "መኾን") ፡ ከሚለው ፡ የግእዝ ፡ አንቀጽ ፡ የተገኘ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ነው ። በትርጓሜው ፡ የአካልን ፡ ህላዌ ፡ ይገልጻል ። የሀገር ፡ ሠሪ ፡ እና ፡ ባለቤት ፡ የኾነው ፡ ዐምሐራ ፡ (ነጻ ፡ ሕዝብ) ፡ ሀገሩን ፡ በነጻ ፡ ፈቃዱ ፡ "ኹን" ፡ ብሎ ፡ የሚከውንበት ፡ ሥርዐት ፡ **"ክዋኔ"** ፡ (Constitution) ፡ ይባላል ፥ በተለምዶ ፡ **"ሕገ ፡ መንግሥት"** ፡ እንለዋለን ።

**"ከዊን"** ፡ ከሚለው ፡ አንቀጽ ፥ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፥ የሚከተሉት ፡ ቃላት ፡ ይገሰሳሉ ፦

**"ከዋኝ"** ፤ የሚከውን ፡ (constituent)

**"ኩነት"** ፡ (በግእዝ) ፡ ወይም ፡ "ኹነት" ፡ (በዐማርኛ) ፤ ህላዌ ፡ ያለው ፡ አካል ፥ መንግሥት ፡ (በእንግሊዝኛ ፡ "State" ፥ ላቲን ፡ "este" ፡ ወይም ፡ "ኾነ" ፡ ካለው ፡ ዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡ የተገኘ ። )

**"ሀገር"** ፤ አንድ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፥ በሰፈረበት ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በሥልጣኑ ፡ የመሠረተው ፡ ግዛት ፤ ወይም ፡ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ሀገር ፡ በሕዝብ ፡ እና ፡ በምድር ፡ መዋሐድ ፡ የሚገኝ ፡ ሐራ ፡ ግዛት ፡ ነው ፥ የሀገር ፡ ባለቤት-ሕዝብም ፡ "ዐምሐራ" ፡ ይባላል ።

**"ዐምሐራ"** ፤ ቃል ፡ በቃል ፡ "ነጻ ፡ ሕዝብ" ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፣ የሀገር ፡ ባለቤት ፣ ሿሚ ፡ ሻሪ ፣ እግዚእና ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ (citizenry) ።

**"እግዚእና"** ፤ ገዢነት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (sovereignty) ፤ አንድ ፡ ነጻ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ እና ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ገዢነት ፡ እንዳለው ፡ ኹሉ ፥ አንድ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐምሐራ ፥ በራሱ ፡ እና ፡ በሀገሩ ፡ ላይ ፡ እግዚእና ፡ አለው ።

**"ሀገራዊ ፡ እግዚእና"** ፤ አንድ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐምሐራ ፡ በሀገሩ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የገዢነት ፡ ሥልጣን ።

**"ሀገራዊ"** ፤ *(በስምነቱ)* ፡ ዐምሐራዊ ፣ የሀገር ፡ ባለቤት ፣ ሿሚ ፡ ሻሪ ፣ እግዚእና ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ አባል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (citizen) ።
*(በቅጽልነቱ)* ፡ የሀገር ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

## 3.2 ፤ ክዋኔያችንን ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ እናድስ ።

የሀገር ፡ ክዋኔ ፡ በባለቤቱ ፡ ሕዝብ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ እግዚእና ፡ የሚፈጸም ፡ ድርጊት ፡ ነው ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ አንድ ፡ ሀገር ፡ በሌላ ፡ መንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ ሊፈጠርም ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፥ በቅኝ ፡ ግዛት ፡ ሥር ፡ የነበሩ ፡ ሕዝቦች ፥ በተለይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብን ፡ የነጻነት ፡ አርኣያነት ፡ በመከተል ፥ ከፊሎቹ ፡ በትጥቅ ፡ ትግል ፡ በፈጸሙት ፡ ተጋድሎ ፡ ሐራ ፡ ሀገርን ፡ ሲመሠርቱ ፥ ከፊሎቹ ፡ ደግሞ ፥ በቅኝ ፡ ገዢዎቻቸው ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ "የውዴታ ፡ ግዴታ" ፥ ሐራ ፡ መንግሥታቸውን ፡ በችሮታ ፡ አግኝተዋል ።

እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያሉ ፡ ሀገሮች ፡ ግን ፥ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ ሠርተዋል ፤ ሐራነታቸውን ፡ እና ፡ እግዚእናቸውን ፡ አስከብረዋል ። የሠሩትን ፡ ሀገራቸውን ፡ ራሳቸው ፡ ካላጠፉት ፡ በቀር ፥ ማንም ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ የሚያጠፋበት ፡ አገባብ ፡ አይኖርም ። ለዚህም ፡ ምክንያቱ ፥ የሀገር ፡ ክዋኔ ፡ በባለቤቱ ፡ በሕዝቡ ፡ የአኂኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የተከወነ ፡ በመኾኑ ፥ ባለቤቱ ፡ ሕዝቡ ፡ ራሱ ፡ ካልፈቀደው ፡ ወይ ፡ ካልተከላከለው ፡ በቀር ፥ በምንም ፡ ዐይነት ፡ በሌላ ፡ የውጭ ፡ አካል ፡ ፍላጎት ፡ ብቻ ፡ ሀገሩ ፡ ስለማይፈርስም ፡ ስለማይታደስም ፡ ነው ።

የታሪክ ፡ መዝገቦች ፡ እንደሚያመለክቱት ፥ ኢትዮጵያ ፡ በርትዕ ፡ ኹነትነት ፡ የተመሠረተችው ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፥ ወይም ፡ የዛሬ ፡ 3000 ፡ ዓመት ፡ ቢኾንም ፥ ራሷን ፡ በሥልጣኔዋ ፡ የሠራች ፡ ሀገር ፡ ስለ ፡ ኾነች ፥ ዐያሌ ፡ ወረራዎች ፡ ቢፈራረቁባትም ፥ ሊያፈርሷት ፡ እና ፡ ሊያጠፏት ፡ አልቻሉም ።

ይህን ፡ እውነት ፡ የተረዳ ፡ አጥፊ ፡ የምልክዮሽ ፡ (የ"ኢምፔሪያሊዝም") ፡ ኀይል ፦ *"ኢትዮጵያ ፡ የምትጠፋው ፡ የሠራት ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ዐምሐራ ፥ በራሷ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተጠቅቶ ፥ ኢትዮጵያዊነቱን ፡ ሲክደው ፡ ብቻ ፡ ነው!"* በሚል ፡ ዐቅድ ፥ ከ 50 ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፥ በኢትዮጵያ ፡ የተፈራረቁት ፡ እና ፡ በምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ የሚዘወሩት ፡ የውንብድና ፡ አገዛዞች ፡ ኹሉ ፥ ዐምሐራን ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ለይተው ፡ የማጥቃት ፣ ክርስቱ ፡ የማፈናቀል ፥ ከሀገሩ ፡ የማባድ ፡ ዘመቻቸውን ፡ በማከታተል ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይፈጽሙበታል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ዐምሐራም ፥ ያልቀማም ፡ ባይ ፡ ታጋይነቱን ፣ ያልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነቱን ፡ በመፈጸም ፥ የፋኖ ፡ ሰራዊቱን ፡ ደርጅቶ ፡ ለመከላከል ፡ ተነሥቷል ። መላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ፋኖን ፡ ፈጥኖ ፡ በመደገፍ ፥ መከላከያ ፡ ክንዱ ፡ እና ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን ፡ ማቋቋሚያ ፡ ኀይሉ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፡ የተፈራረቁብን ፡ የውንብድና ፡ አገዛዞች ፡ የ 3000 ፡ ዓመት ፡ ዐፄ-ሥራችንን ፣ ሥርዐተ ፡ መንግሥታችንን ፡ ሽረው ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ ረምርመውብናል ። እኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በፋኖነት ፡ የምንታገለው ፡ እንደሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባለቤትነታችን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ እስከታገልን ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኹነት ፡ ተጠብቆ ፡ ይኖራል ፤ ሀገር ፡ ኢትዮጵያም ፡ እንደ ፡ ዩጎስላቭያ ፡ አትፈርስም! የሚፈርሰው ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የተባለው ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ከእንግዲህ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ትድግና ፡ በኹለት ፡ መንገድ ፡ ሊከናወን ፡ ይችላል ፦

- ወይ ፡ በፋኖ ፡ ትግል ፡ ነጻ ፡ የሚወጡትን ፡ ግዛቶች ፡ በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ምሕቃፍ ፡ ውስጥ ፡ በማስገባት ፥ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መላ ፡ ሀገሪቱን ፡ ነጻ ፡ ማውጣት ፤
- ወይም ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ በሚፈጸም ፡ አጠቃላይ ፡ ሕዝባዊ ፡ መነሣት ፥ መላ ፡ ሀገሪቱን ፡ ነጻ ፡ ማውጣት ።

ነጻ ፡ የምትወጣዋ ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፥ በዐዲስ ፡ ክዋኔ ፡ የምትከወነው ፥ መላ ፡ ሕዝቧ ፡ በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱ ፡ የበላይ ፡ ጠባቂነት ፥ ተወካዮቹን ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንገድ ፡ በመሠየም ፥ ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤውን ፡ ሲመሠርት ፡ እና ፥ በተወካዮቹም ፡ አማካይነት ፥ መክሮ ፡ ዘክሮ ፥ ዐዲሱን ፡ ክዋኔውን ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ሲያረቅ ፡ እና ፡ በሕዝባዊ-ፈረዳ ፡ ሲያጸድቀው ፡ ይኾናል ።

ይህን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ኺደት ፡ የምንመራበትን ፡ ስልት ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፦

"ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡
ሀገራዊ ፡ ቅያስ ። "

በተሠኘ ፡ ሰነዱ ፡ ለሕዝብ ፡ ስሜት ፡ አቅርቦታል ፥ ፈጥነን ፡ ሀገራችንን ፡ እንታደግበት ፡ !

---

ስለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ አመሠራረት ፡ እና ፡ ስለ ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦቹ ፡ በቂ ፡ መረጃን ፡ ከመርበቢያው ፡ ከ ፦

www.slttunhzb.net

ማግኘት ፡ ይቻላል ።

ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

የመብት ፡ አባል ፡ ነው ፤ በመብቱ ፡ መሥራቱን ፡ ወይም ፡ አለመሥራቱን ፡ የራሱ ፡ ምርጫ ፡ ይወስነዋል ።

---

ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዐላማ ፥ ማለት ፦

1ኛ ፤ ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ ማስከበር ፤
2ኛ ፤ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ መሥራት ፤
3ኛ ፤ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥታችንን ፡ መመሥረት

ሦስት ፡ ረድፎች ፡ ውስጥ ፡ ኹለቱን ፡ እንሆ ፡ ተንትነናል ። ሦስተኛውን ፡ እና ፡ የመጨረሻውን ፡ ረድፍ ፡ በሚቀጥለው ፡ ጦማር ፡ እንተነትናለን ።

ጦማሮቹ ፡ ኹሉ ፥ እዚሁ ፡ እኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መርበቢያ ፡ እ ፦

www.slttunhzb.net

ላይ ፡ ይገኛሉ ።

ሙሉ ፡ መረጃን ፡ የሚሰጡ ፡ ሌሎች ፡ ሰነዶች ፡ ዐብረው ፡ አሉላችኹ ፤ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ሥራው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ብዘውን ፡ ጕዳይ ፡ በዝርዝር ፡ ዐትቶላችኋል ።

አስተያየትን ፡ ወይም ፡ ጥያቄን ፡ በቀጥታ ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መላክ ፡ ለምትሹ ፡ ደግሞ ፡ በእ-ጦማር ፡ አድራሻው ፡ በ ፦

sh1@ttomar.net

ልትጽፉለት ፡ ትችላላችኹ ።

[ ጦማሮቹ ፡ ኹሉ ፡ የሚጻፉት ፡ በትኽክለኛው ፡ የፊደል ፡ አጠነቃቀቅ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶችን ፡ ለማስወገድ ፡ ሞክረናል ፥ ለዚህም ፡ **ዐውደ-ቀለም** ፡ የተባለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ (software) ፡ ረድቶናል ፤ እናንተም ፡ እንድትሠሩበት ፡ እናበራታችኋለን ።

መገኛው ፦

www.awde-qelem.net ፡ ነው ፥
በ Windows ፡ ምግባር ፡ (operating ፡ system) ፡ ላይ ፡ ይሠራል ። ]

---

### የቃላት ፡ መፍቻ ፤

**ሀገር** ፤ በራሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ የተሠራ ፥ እግዚእና ፡ ያለው ፡ ሐራ ፡ ግዛት ፡ (Civilisation-State) ።

**ሀገራዊ** ፡ ( ስም ) ፤ የሀገር ፡ ሠሪ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ ዐምሐራዊ ፡ (citizen, *n.*)

**ሀገራዊ** ፡ (ቅጽል) ፤ የሀገር ፥ ዐምሐራዊ ፡ (citizen, *adj.*)

**ሕዝባዊ-ፈረዳ** ፤ ውሳኔ-ሕዝብ ፡ (referendum)

**መርበቢያ** ፤ የመረብ ፡ ገጽ ፡ መገኛ ፡ (web site)

**ሥልጡን** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ (civil)

**ሥልጡንሕዝባዊ** ፤ የሥልጡንሕዝብ ፡ (democratic)

**ሥልጡንሕዝብ** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ ሕዝብ ፡ (democrat)

**ሥልጡንሕዝብና** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፥ አንዱ ፡ የሌላ ፡ ብጤውን ፡ መብት ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ በሀገርንት ፡ ዐብሮ ፡ የሚኖርበት ፡ ሥልጡን ፡ ሥርዐት ፡ (democracy)

**ስያስ** ፤ ዘዴ ፡ (policy)

**ስያሳ** ፤ "ፖለቲካ" ፡ (politics)

**ስያሳዊ** ፤ "ፖለቲካዊ" ፡ (political)

**እግዚእና** ፤ ገዢነት ፡ (sovereignty)

**ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊነት ፡ ያለው ፥ ዐምሐራዊ ፡ (Ethiopian citizen)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

**እ-ጦማር** ፤ እለቁጥሯዊ ፡ ወይም ፡ ንምራዊ ፡ ጦማር ፥ መልክት ፡ (e-mail)

**ከወነ** ፤ ኹነትን ፡ ወይም ፡ መንግሥትን ፡ ኾነ ፣ ተሠራ ፣ ተመሠረተ ፣ ቆመ ፣ ጸና ፡ (to be constituted)

**ከወነ** ፤ ኹነትን ፡ ወይም ፡ መንግሥትን ፡ ሠራ ፣ መሠረተ ፣ አቆመ ፣ አጸና ፡ (to constitute)

**ከዋኝ** ፤ የሚከውን ፣ አኳኝ ፡ (constituent)

**ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፤ የሀገርን ፡ ክዋኔ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለማርቀቅ ፡ እና ፡ ለማጽደቅ ፥ በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንገድ ፡ በሕዝብ ፡ የተሠየመ ፡ የተወካዮች ፡ ጉባኤ ፡ (constituent assembly)

**ክዋኔ** ፤ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ (Constitution)

**ኹነት** ፤ (በግእዝ ፥ ኩነት) ፡ ህላዌ ፡ ያለው ፡ አካል ፥ መንግሥት ፡ (State)

**ዐምሐራ** ፤ ዐም ፡ = ፡ ሕዝብ ፥ ሐራ ፡ = ፡ ነጻ ፥ በተገናኝ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ እግዚእና ፡ ያለው ፥ የሀገር ፡ ሠሪ ፥ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ (citizenry)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( *ስም* ) ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ የዐምሐራ ፡ አባል ፥ ሀገራዊ ፥ አገሬ ፡ (citizen, *n.*)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( *ቅጽል* ) ፤ የዐምሐራ ፥ የሀገር ፡ (citizen, *adj.*)

**ጦማር** ፤ መልክት ፡ (mail ፡ ወይም ፡ post)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።